# የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ህብረት(ደምኢሕህ) መቋቋምን አስመልክቶ የወጣ መግለጫ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያሕዝቦች በቀድሞ ካፋ ክፍለ ሀገርና በካፋ አስተዳደር አካባቢ የሚገኙ ሕዝቦችን ያጠቃልላል። ከክልሉ ነዋሪ ሕዝቦች ባሻገር በተለያዩ ወቅቶችና ምክንያቶች ለምሳሌ፥በመኖርያ አካባቢ ምርጫ፣ በስራ፣ በሰፈራ ወዘተ መጥተው በአካባቢው ነዋሪ የሆኑኢትዮጵያዊያን ዜጎች ይገኛሉ።

ይህ አካባቢ በአንድ ወቅት እስከዛሬ ታሪክ ከምያወድሳቸው ጠንካራ ህዝቦችና መንግስታዊ ሥርዓት የተገነባና በሀብት የበለፀገ አካባቢ ነው።አካባቢው በምድርና በከርሰ ምድር ሃብት የታደለ ከመሆኑም በተጨማሪ በዓለም ላይ በጥብቅ ደን ማዕከልነት ተመዝግቦ የዓለምን የአየር ፀባይ በመቆጣጠር ረገድ ጉልህ ድርሻ ይዞ የሚገኝና፥ ለአገራችን ኢትዮጵያም ወሳኝ የምጣኔ ሃብት አውታር ሆኖ የዘለቀ ነው።ሕዝቦቹም ለሀገር አንድነትና ዳር ድንበር መከበር ሲሉ በርካታ መሥዋዕትነትን ሲከፍሉ የኖሩ ጀግና ሕዝቦች እንደሆኑ ታሪክ ይመሰክራል።

ይህ ሆኖም በኢትዮጵያ ሲፈራረቅ በመጣዉ የጨቋኝ ሥርዓት ምክንያት አንድም ቀን ሕዝቡ የራሱን ነፃ ዕድል ለመወሰንና በሀብቱም ሊጠቀም አልታደለም። አሁን ይባስ ብሎም የሕወሃት ስርዓት የራሱና የማንነቱ መግለጫ የሆነዉ ለም መሬትና የተፈጥሮ ሀብቱን ነጥቆ ሕዝቡን ወደ ድህነት ዉስጥ ከቶ ይገኛል። ለምን ብሎ ጥያቄ ለማንሳት የሞከረ ሁሉ እሥር ቤት ገብቷል፤ ተሰደዋል አልያም ተገድለዋል።

ለዘመናት የዘለቀዉ ይህ በደልና ግፍ ከእንግዲህ ወዲህ መቀጠል የለበትም። የሕብረተሰቡ ምሬት ጫፍ ደርሷል።የሀገሪቱዋ መላ ሕዝብም ለዴሞክራሲ፣ለፍትህ እና ለነፃነ ከፍተኛ መሥዋዕተነት በመክፈል ላይ ይገኛል።

መላዉ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችም በተለያየ ጊዜ በተናጠል ሥርዓቱን ሲታገሉ ሰንብተዋል። አሁንም በመታገል ላይ ናቸዉ። ሆኖም ሕወሃት በተደራጀ መንገድ የሚፈፅመዉን ሀገራዊ በደል በተናጠል መታገል ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ አንድ ጠንካራ ፖለቲካዊ አደረጃጀት መፍጠርና ከሌሎች ወገኖች ጋር ይህንን በዝበዥና ኢሰብአዊ ሥርዓት መታገል አስፈላጊነቱን አምነን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ህብረትን ወይም ደምሕኢህን መሥርተናል።

ደምኢሕን የደቡብ ምዕራብ ሕዝቦችን በማስተባበር በሀገሪቱዋ በሚደረገዉ የደሞክራሲ ትግል ዉስጥ ሕዝቡ በተደራጀ መልክ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግና መብቱን በማስከበር የሃብቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆን ጠንክሮ ሕዝቡን ያስተባብራል፣ያደረጃል ።ለዚህም ዓላማ ስኬት ከማንኛዉም ዓላማችንን ከሚደግፉ የኢትዮጵያ ቡድኖችና ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆናችንን ልንገልፅ እንወዳለን።

***ፍትህ፣ነጻነት፣እኩልነት እና ዴሞክራሲ ለህዝቦቻችን!***

***የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ህብረት አስተባባሪ ኮሚቴ***

**ጥር 2009 ሴሜን አሜሪካ**